## የዳሰሳ ጥናት

# በኢትዮጵያ የጉምሩክ አሰራርና የሎጅስቲክ ጉዳዮች ዙሪያ የሚስተዋሉ አንዳንድ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች

አዘጋጅ ፡ የኢትዮጵያ የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ፡ 2004 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ ማቋቋሚያ ሠነድ ከተፈረመ እነሆ ከአንድ ዓመት በላይ አስቆጠረ። ይህ ሠነድ ከተፈረመ በኋላ የመጀመሪያው የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ በየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ተደርጓል።

በዚህ መድረክም የተለያዩ መግባባቶች ላይ የተደረሰ ሲሆን እነዚህንም ለማስፈጸም የኢትዮጵያ የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው የመንግስት ሃላፊዎች ጋር በመሆን አፈጻጸሙን ሲከታተል ቆይቷል።

በዚህም መሰረት ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች የአፈጻጸም ሁኔታ ምን ላይ እንደደረሰ ያጣራ ሲሆን ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮች ግን በበለጠ ሁኔታ ተጠንተው እና አግባብ ያላቸው የመፍትሄ ሃሳቦች እንዲቀርቡ የቴክኒካል ቡድን ለማዋቀር ከሚመለከታቸው ሃላፊዎች ጋር አብሮ እየሰራ ይገኛል።

ከዚህ ባሻገር ሁለተኛው የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም ለማድረግ የታሰበ ሲሆን ለዚህም አስፈላጊውን ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። በመሆኑም የጉምሩክና የአሰራር ሥርዓት የተቀላጠፈና አጭር ለማድረግ ሊረዱ ይችላሉ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጽ/ቤቱ የዳሰሳ ጥናት አድርጓል። ይህ ጉዳይም በሁለተኛው የፌዴራል የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ አጀንዳ ሆኖ እንዲቀርብ ታስቧል።ይህ የዳሰሳ ጥናት ለምክክር መድረኩ ለማብቃት ሰነዶችን በማገላበጥና ባለድርሻ አካላትን በማነጋገር የተካሄደ ነው። ለታለመለት ግብና ለውይይት በቂ መነሻ ነው ።

ይህ ጉዳይ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት የጉምሩክና ሌሎች የሎጅስቲክ አገልግሎቶች ለውጭ ንግዳችንም ሆነ ለጠቅላላ የምጣኔ ሃብት ዕድገታችን ከፍተኛ አስተዋፆ ስላላቸው ነው።

በርግጥም የጉምሩክ ሥራ በባህሪው በፍጥነት ተለዋዋጭ በመሆኑም በመስኩ የተሰማሩ ሙያተኞች ንግድን ለማቀላጠፍ እና የመንግስትን ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም የሚያስችሉ እርምጃዎች ሚዛናቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የንግድ ሥራዎች በወጪ እና ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ላይ መስተጓጐል እንዳይደርስባቸው እንዲሁም የመንግስት ህጋዊ የቁጥጥር ተግባራት እና ገቢዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳይከተል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ዘላቂነት ያለውና በመተማመን ላይ የተመሰረተ ሽርክና በመፍጠር ሥራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

**2. የተቀላጠፈ የጉምሩክ አሰራር መርሆዎች**

***ሀ. ግልፅነት***

የጉምሩክ አሰራር የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ ከሚያስፈልጉት ዋነኛ መርሆዎች መካከል ግልፅነት የሰፈነበት አሰራር እንዲኖር ማድረግ አንዱና ቁልፉ ነው፡፡ በጉምሩክ አሰራር ግልፅነት ማለት ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስፈለጉትን መረጃዎች፣ መስፈርቶች እንዲሁም ስነስርዓቶች ግልፅ በሆነና በማያሻማ መልኩ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ በሚችል መልኩ ማሰቀመጥ ማለት ነው፡፡

ይህንንም ተግባራዊ ለማደረግ አገራት የተለያዩ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ሲሆን በአሁኑ ግዜ በብዛት እየተተገበረ ያለው እነዚህን ጠቃሚ መረጃዎችና የህግ ሰነዶች በድረ-ገጽ ላይ ማስፈር ነው፡፡

**ለ.ቀላል የሆኑ የህግ፤የሰነድና አስተዳደራዊ መስፈርቶችን ማሰቀመጥ**

የጉምሩክ አሰራር የተቀላጠፈና አጭር እንዲሆን ከሚረዱ መርሆዎች መካከል የጉምሩክ አስተዳደራዊና የሰነድ መሰፈርቶች በቀላሉ የሚሟሉ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ነጋዴ ወደ አገር ውሰጥ ለማስገባትም ሆነ ሆነ ከአገር ውጭ ለመላክ የሚጠየቀው የሰነድ ዓይነት በቁጥርም ሆነ በይዘት አግባብነት ያለውና አስፈላጊነቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

ሐ. **የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም**

አሁን ባለንበት ዓለም አገራት ዕድገታቸው ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በምንያህል ደረጃ መጠቀማቸው ነው፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተቀላጠፈና የተቀናጀ አገልግሎት ለመስጠትም ሆነ ለስራው ጥራት ያለው ሚና የጎላ ነው፡፡ ስለሆነም ለጉምሩክ የተቀላጠፈ አሰራር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በበቂ ሁኔታ መጠቀም አግባብነት ይኖረዋል፡፡

3. **የተቀላጠፈ የጉምሩክ አሰራር ጥቅሞች**

የተቀላጠፈ የጉምሩክ አሰራር መዘርጋት ኢያሌ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል፡፡

- **ተወዳዳሪነትን ለመጨመር**

የአስመጭዎችም ሆነ የላኪዎች ተወዳዳሪነት በሚያወጡት ወጭ እንዲሁም ስራቸውን ለማከናወን በሚወስድባቸው ግዜ ይወሰናል፡፡ አንድ አገር የተንዛዛ የጉምሩክ አሰራር የምትከትል ከሆነ በነጋዴዎች ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በተቃራኒው የተቀላጠፈ አሰራር የዘረጋች እንደሆነ በዘርፉ

ለተሰማሩ ከአላስፈላጊ ወጭና የግዜ ብክነት መታደግ ይቻላል፡፡ ይህም በሚሆን ግዜ ተወዳዳሪነታቸው ይጨምራል፡፡

- **የመንግስት ገቢን በአግባቡ ለመሰብሰብ**

የጉምሩክ አሰራር የተደራጀና በኢንፎርማሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እንደሆነ መንግስት ከዘርፉ ለያገኘ የሚገባውን ገቢ በቀላሉ ለመሰብሰብ ይችላል፡፡

- **ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል**

የጉምሩክ አሰራር የተቀላጠፈ መሆን ብዙዎችን በሕጋዊ መንገድ ነግደው ለማትረፍ ከማነሳሳቱም በላይ በዚህ ምትክ ሊስፋፋ የሚችለውን ሕገ-ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድን በተሻለ ሁኔታ ለመቆጣጠር ብሎም ለማጥፋት አጋዥ ሚና ይኖረዋል፡፡

- **የሕብረተሰቡን እንዲሁም የዕፅዋትንና የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅ**

  የተቀናጀ የጉምሩክ አሰራር፤ አስፈጻሚ የመንግስት ባለድርሻ አካላት ለሚያደርጉት የቁጥጥር ስራ አጋዥ ከመሆኑም በላይ በሚፈጠር ክፍተት በህበረተሰቡ እንዲሁም በእንስሳትና ዕፅዋት ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመቆጣጠር ይረዳል፡፡

**4. የጉምሩክ *ሥነሥርዓት* አፈጻጸም ሂደት**

በኢትዮጵያ የገቢዎችንና የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የተደነገገዉ አዋጅ ቁጥር 60\97 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 19 መሠረት የጉምሩክን ሥነሥርዐትን እንዲህ ሲል ተርጉሞታል፡-

“ወደ አገር የሚገባ ወደ ዉጭ የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ የጉምሩክ አፈጻጸም ሂደት በጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እንደ አግባብነቱ አሰመጪዉ እሰኪረከበዉ ወይንም ከኢትዮጵያ እሰከሚወጣ የሚከናወን ማናቸዉም የጉምሩክ አፈጻጸም ሂደት”

በዚህም መሰረት ወደ ኢትዮጵያ ለሚገባ ዕቃ ከወደብ ተነስቶ ኢትዮጵያ እስከሚገባ ድረስ ሊያልፍበት የሚገባ ጉምሩክ ሥነሥርዓቶች አሉ፡፡

የሚከተሉት ስዕላዊ መግለጫዎች እነዚህን ሥነሥርዓቶች በግልጽ ያስረዳሉ፡፡

## <u>ዕቃዉ ከጅቡቲ ወጥቶ መጋዘን(ኢትዮጵያ) እስኪገባ ድረስ ያፈጻጸሙ ሂደት እና የሚያሰፈልጉ ሰነዶች</u>



**<u>ዕቃዉ ከመጋዘን ወጥቶ አስመጪዉ እስኪረከበዉ ድረስ ያፈጻጸሙ ሂደት እና የሚያስፈልጉ ሰነዶች</u>**

| | |
|---|---|
| የባንክ ፈቃድ | • L/C የተፈቀዴበት<br>• ዴቢት አድቫይስ(የተጠቀመበትን ዶላር የሚያሳይ ደረሰኝ) |
| የዋጋ ሰነድ | • የተረጋገጠ የዋጋ ሰነድ (chamberized) |
| የማጓጓዣ ሰነድ | • ኦሪጅናል ኮፒ |
| የተመረተበት አገር ማረጋገጫ ሰነድ | • በቻምበር የተረጋገጠ |
| ዕቃዉ ማሟላት ያለበት ሰታንዳርድ የሚመሰክር ሰነድ | • አስመጪዉ መድኃኒት መብል ወይም ኤሌክትሮኒክስ እና የመሳሰሉት ዕቃዎች ሲያስገባ ከሚመከለተዉ የመንግስት አካል የጥራት ፈቃድሰ ያሰፈልገዋል |
| ቫት የተመዘገቡበት ሰርተፊኬት | • አስመጪዉ ቫት የተመዘገበበት |
| የንግድ ፈቃድ | • የአስመጪዉ የንግድ ፈቃድ ኮፒ |
| የዕቃ ዝርዝር | • ኢምፖርት የተደረገዉ ዕቃ ዝርዝር ከነዋጋ<br>• ዕቃዉ እንዴት እንደታሸገ |

**እነዚህ ሰነዶች ፌስ ቬት ክፍል ይቀርባሉ**

ሰነዶቹ የተሟሉ ከሆነ ፌስ ቬቱ አፕሩቭ ይደረግና መዝገቡ ወደ ተመደበዉ ፈታሽ(አሴሰር) ያተላለፋል

ሰነዶቹ ካልተሟሉ ፌስ ቬቱ ሪጀክት ይደረጋል

በሪሰኩ መሰረት ፈታሹ ሰነዱንና ዕቃዉን ፈተሾ (ቀይ ከሆነ) ወይም ሰነዱን ብቻ ፈትሾ (ቢጫ ከሆነ) ወይም ሳይፈትሽ (አረንጓዴ ከሆነ) ዕቃዉን ለአስመጪዉ ያስረከባል:

## 5. በጉምሩክ አሰራርና ሎጂስቲክስ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአንድ አገር የውጭ ንግድም ሆነ የአገር ውስጥ ንግድ ላይ የጉምሩክ አሰራር ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫወታል። ይህንንም በመገንዘብ አገራት የጉምሩክ አሰራራቸውን የተቀላጠፈና አጭር በማድረግ ወደ አገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚላኩ እቃዎችን በተፋጠነ አሰራር የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ፈጥረዋል። አገራችን ኢትዮጵያም ባለፉት ጥቂት አመታት የጉምሩክ አሰራርን በተወሰነ ደረጃ ለማሻሻል ጥረት ስታደርግ ቆይታለች። በተለይም የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ከሆነ ጀምሮ የጉምሩክ አሰራር መሻሻል ማሳየቱን በዘርፉ የተሰማሩ የባለድርሻ አካላት ያስረዳሉ።

ይሁንና አሁንም ቢሆን የነጋዴውን ማህበረሰብ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ የሚያረካ አሰራር ተዘርግቷል ለማለት አያስደፍርም። ይልቁንም ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት መተግበር ያለባቸው የጉምሩክ ስነስርዓቶች በተቀላጠፈ፡ አጭርና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እየተፈጸሙ አይገኝም። ለዚህም የጉምሩክ ውስጣዊ አሰራርም ሆነ ሌሎች የመንግስትና  የግልዘርፍ የባለድርሻ አካላት አስተዋፆ ያደርጋሉ። በርግጥም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድርጅት ከተለያዩ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ጋር የሚሰራ ተቋም እንደመሆኑ ሌሎች እህት ድርጅቶች ስራቸውን በተፋጠነ ሁኔታ ያለመፈጸም በጠቅላላ አገልግሎቱ ላይ አሉታዊ ተጽኖ ይኖረዋል። በዚህና ሌሎች የውስጥ ችግሮች የተነሳም የጉምሩክ ስነስርዓት አጭርና የተቀላጠፈ እንዳይሆን ሲያደርጉት ይታያሉ።

ይህ የጉምሩክ አገልገሎት የተፋጠነና ቀልጣፋ አለመሆን ደግሞ አገራችን እያከናወነችው ያለውን ፈጣን የዕድገት ጉዞን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመግታት አቅም አለው። በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ የንግድ መጠን ከፍተኛ የሚባል አይደለም።  እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2010 ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የላከችውን መጠን ብንመለከት 1626.9 ሚሊዮን ቶን ሲሆን በአንጻሩ 7051.5 ሚሊዮን ቶን ዕቃ ለማስገባት ችላለች። ይህ መጠን ከሌሎች አገራት አንጻር ሲታይ ትንሽ ሊባል የሚችል ሆኖ ይህንንም መጠን ያህልም ቢሆን በፍጥነት የሚሰተናገድበት ሁኔታ የለም። በዚህም የተነሳ ዓለም ባንክ በየአመቱ በሚያወጣው የንግድ አሰራር ደረጃ ኢትዮጵያ ከግማሽ በታች ባለው ተርታ ትገኛለች። ይህም ከሆነባቸው ምክንያቶች ውሰጥ በዋቢነት የሚጠቀሰው ከኢትዮጵያ ዕቃዎችን ወደ ውጭ ለመላክ እንዲሁም ለማስገባት የሚፈጀው አማካይ ግዜ ከፍ ያለ መሆን ነው።

በግል ዘርፍ ማበልጸጊያ ማዕከል በጉምሩክ ስርዓት ዙሪያ በ2003 ዓ.ም ተጠቃሎ በተሰራጨው ዕትም መሰረት ጭነት ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚደረገው የሰነድ ዝግጅት፣ የአገር ውስጥ ትራንስፖርት እንዲሁም የጉምሩክ ስነስርዓትን ለማጠናቀቅ በአማካኝ 27 ቀናት ይፈጃል። የዓለም ባንክ እኤአ በ 2011 ያወጣው ሪፖረት እንደሚያትተው ከሆነ ደግሞ በአማካይ እስከ 44 ቀናት ሲፈጅ የሰሃራ በታች አገራት

አማካኝ ግዜ ግን 37 ቀናት እንደሆነ ይህ ጥናት ይደመድማል። የዓለም ባንክ ሪፖርት ከኢትዮጵያ ጭነት ወደ ውጭ ለመላክ በአማካይ 42 ቀናት የሚፈጅ መሆኑን አስቀምጦ፣ ይህ ግዜም ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች ከሚወስድባቸው 32 ቀናት ትርጉም ባለው ደረጃ ከፍ ይላል። ሁለቱንም ስራዎች በዝርዝር በምንቃኝበት ግዜ በግል ዘርፍ ማበልጸጊያ ማዕከል የተሰራው ለእውነታው ቀረቤታ ያለው ይመስላል። በየትኛውም መለኪያ ግን ከውጭ ዕቃዎችን ለማስገባት የሚፈጀው ግዜ /27 ቀናት/ ከፍ ያለ ነው። በተጨማሪም በዚህ ጥናት መሰረት አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈፅሞበት ከጉምሩክ ጣቢያ እስከሚወጣ ድረስ በአማካይ እስከ 13.7 ቀናት ያህል እንደሚፈጅበት ያትታል።

ከላይ በተጠቀሰው በ 2003 ዓ.ም ተጠቃሎ በተሰራጨው የግል ዘርፍ ማበልጸጊያ ማዕከል ዕትም መሰረት ዕቃ ከጉምሩክ ሳይወጣ ለአንድ ቀን ያህል እንኳን ቢዘገይ የ 0.8% አድቫሎረም ቀረጥ ያህል ውጤት ይኖረዋል። ይህ ወጪ ደግሞ የግል ዘረፉን ተወዳዳሪነት ምንኛ ሊጎዳው እንደሚችል መረዳት አያዳግትም። ከዚህም በላይ በዚህ በሚፈጠር ኪሳራና መጉላላት ምክንያት ብዙዎች የጭነት አስተላላፊዎች የደንበኞችን ዕርካታ ያጣሉ።

በርግጥም ከላይ የተጠቀሱትን የአማካይ ግዜያትን የሚያረዝሙና የሚያሳጥሩ የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ። ለአብነትም አንድ አገር ከወድብ ያላት ቅርበት እንዲሁም የትራንስፖርት ዘርፉ ዕድገት ጉልህ ሚና ሊጫወት ይችላል። ኢትዮጵያ ከወደብ ያላት እርቀትም ሆነ ያልዳበረው የትራንስፖርት ዘርፍ አገልግሎት ለሚወስደው የአማካኝ ግዜ መጨመር እንደ ምክንያት ለጠቀሱ ይችላሉ።ይህንን ታሳቢ ተደርጎም ቢሆን የጉምሩክ አሰራር በተቀላጠፈ ሁኔታ እየተፈጸመ አይገኝም ።

በተጨማሪ የተቀላጠፈ የጉምሩክና የሎጅስቲክ አገልግሎት እንዳይኖር በግል ዘርፉ የሚታዩ ቀላል የማይባሉ ችግሮች የራሳቸው የሆነ ሚና ይጫወታሉ። ለአብነትም የአንዳንድ አስመጪዎች፤ ጭነትና ጉምሩክ አስተላላፊዎች በታማኝነት ዲክላራሲዎን አለመሙላት፤ የተሟላ ሰነድ ይዞ በወቅቱ አለመቅረብ፤ ለመንግስት የሚገባን ክፍያ ላለመክፈል ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት ውስጥ መግባት የማጭበርበር ስራ ማድረግ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ይህን የግል ዘርፍ ችግር ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር አብሮ በመስራት የሚፈታ ሲሆን በዚህ ሰነድ ግን መንግስት ሊያስተካክላቸው ይገባል ያልናቸውን ጉዳዮች ለመጠቆም እንወዳለን። በንግድ ማህበረሰቡ በኩል ሊስተካከሉ ይገባቸዋል የሚባሉት የህግና አፈጻጸም ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ሀ/ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልገሎት ሥርዓት ትግበራና አፈጻጸሙ በዘርፉ በግል ለተሰማሩ የዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎችን (freight forwarding and ship agency) የማያሳትፍ መሆኑ**

መልቲሞዳል ትራንስፖርት ማለት ወጥ በሆነ የትራንስፖርት ውል መሰረት ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶች በመጠቀም በክፍያ እቃን ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ወስዶ ማስረከብ ማለት ነው። ይህ አሰራር በብዙ አገራት የተለመደ ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን ተግባራዊ መሆን የጀመረው ከሚያዝያ 1 ቀን 2001 ዓም ጀምሮ ነው። ይህም አገልግሎት ተግባራዊ የሆነው የአገራችንን ገቢና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ በተረጋገጠ፡ ቀልጣፋ ፡ዘመናዊ እና ወጪ ቆጣቢ የትራንዚት ትራንስፖርት አገልገሎት እንዲስተናገድ ለማድረግ የሚቻልበትን ሥርዓት ለመዘርጋት ነው። በዚህ ስርዓት የሚጠቀሙ ተገልጋዮች በአንድ ሰነድ እቃው ከሚነሳበት አገር ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ የደረቅ ወደብ እስከሚደርስ ድረስ ያለውን አገልገሎት ባንድ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ኦፕሬተር አማካኝነት እንዲፈጽሙ ያስችላቸዋል። ይህም ስርዓት በትራንዚት ትራንስፖርት ምክንያት የሚፈጠረውን አላስፈላጊ ወጪና የጊዜ ፍጆታን በእጅጉ ይቀንሳል። ከዚህም በላይ ከዚህ ቀደም በጂቡቲ ወደብ እቃ ቶሎ ባለመነሳቱ ይከፈል የነበረውን የወደብ ኪራይ ያስቀራል። በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አሰራር የሆነ እንደሆነ እቃው ምንም ዓይነት የጉምሩክ ስነስርዓት ጂቡቲ ላይ ሳይፈጸምበት በቀጥታ ወደ ደረቅ ወደብ እንዲመጣ ይደረጋል። ይህም ወጪን ከመቆጠቡም በላይ የውጭ ምንዛሬንም ያድናል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች የሚያስገኛቸውን ጥቅሞችን በመረዳት የፌዴራል የትራንስፖርት ሚኒስቴር ከላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ ለሙከራ ያህል የመንግስት ተቋማት የሚያስመጧቸው የኮንቴይነርና ተሽከርካሪ እቃዎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት እንዲጓጓዙ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በዚህ የሙከራ ግዜም መልቲሞዳል የታሰበውን ያህል ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል ተረጋግጧል ። ይህም በመሆኑ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ወደተሟላ ትግበራ እንዲሸጋገር ለማድረግና አሰፈላጊውን የአሰራር ሥርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን የትራንስፖርት ሚኒስቴር መመሪያ አውጥቷል።

በዚህ መመሪያ መሰረትም ከታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የመንግስት ተቋማት የሚያስመጧቸው ጄኔራል ካርጎ ገቢ ዕቃዎች በሙሉ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዘው መድረሻ ጣቢያቸው በአገር ውስጥ ደረቅ ወደቦችና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈቃድ በሰጠባቸው የማከማቻ ሥፍራዎች እንዲስተናገዱ አዝዟል። በተመሳሳይ መልኩም ክብደታቸው 3ቶንና ከዚያ በታች የሆኑ ተሽከርካሪ ገቢ ዕቃዎች፤ የመንግስት ባንኮች የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የግል አስመጪዎች የሚያስመጧቸው የኮንቴይነር እቃዎች በሙሉ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት እንዲጓጓዙ በመመሪያ ወስኗል ።

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ተግባራዊ መሆን ለአስመጪዎችም ሆነ ለላኪዎች የሚያስገኘው ጥቅም እንዲሁም በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። **ስለሆነም የግሉ ዘርፍ የዚህን እርምጃ በጎ ጎኖችን ያደንቃል።** ይሁንና የዚህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆን የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅትን በዘርፉ ብቸኛ ተዋናይ የሚያደርገው ሲሆን በተቃራኒው በግል የዕቃ አስተላላፊነትና የመርከብ ውክልና ተሰማርተው የሚገኙትን ከገበያ ውጭ ያደርጋል።

በግል ዘርፉ በዕቃ አስተላላፊነትና የመርከብ ውክልና ተሰማርተው የሚገኙት ደግሞ ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት እየሰጡ የቆዩ መሆናቸው አይካድም። በአገር ውስጥ ወይም በአለምአቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ስነስርዓት፡ የወደብ ስነስርዓት እና ሌሎች ስነሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ በማድረግና ዕቃን በማጓጓዝና በማስረከብ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

በተጨማሪ የመርከብ ባለንብረትን፡ተከራይን ወይም ኦፕሬተርን በመወከል መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛን የማግኘትንና የመመዝገብን፡ ዕቃ የመጫንና የማራገፍን እንዲሁም ዕቃን አጓጉዞ የማከማቸትን ስራ ማስተባበርን እየሰሩ ይገኛል።

በአሁኑ ሰዓት ወደ 78 የሚደርሱ በዕቃ አስተላላፊነትና የመርከብ ውክልና ተሰማርተው የሚገኙ ነጋዴዎች ሲኖሩ እነዚህ በኢትዮጵያ የተሳለጠና የተቀላጠፈ የትራንዚትና የጉምሩክ አገልገሎት እንዲኖር ለማስቻል የሚደረገውን እርብርብ በእጅጉ ያግዛሉ።

መንግስት እቃ ወደ አገር ውስጥ የማስገባትን ከፍተኛ ድርሻ የያዘ መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ የመንግስት ጭነትን ማስተላለፍም ሆነ ማጓጓዝ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የሚሰራው የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ነው ። ከዚህም ባሻገር ከላይ እንደተጠቀሰው ክብደታቸው 3ቶንና ከዚያ በታች የሆኑ ተሽከርካሪ ገቢ ዕቃዎች፣ የመንግስት ባንኮች የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የግል አስመጪዎች የሚያስመጧቸው የኮንቴይነር እቃዎች በሙሉ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት እንዲጓጓዙ በመመሪያ ወጥቷል። በአሁኑ ግዜም ብቸኛው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ኦፕሬተር የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በመሆኑ በግል ዘርፍ በዕቃ አስተላላፊነትና የመርከብ ውክልና ተሰማርተው የሚገኙትን የገበያ ደርሻ በእጅጉ ያጠበበ ከመሆኑም ባሻገር መመሪያው የግል ዘርፉ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የሚሳተፍበትን ሁኔታ አያስቀምጥም። በዚህም የተነሳ ብዙዎች ከገበያ ውጭ የመሆናቸው ስጋት አይሏል።

የግሉ ዘርፍ በዚህ ስርዓት መሳተፉ የፈጠረውን የስራ እድል የሚያስጠብቅና ወደፊትም ተጨማሪ ዕድል የሚያስከፍት ከመሆኑም ባሻገር የአገልግሎት አሰጣጡ ውድድር የተሞላበትና በበቂ ሁኔታ እንዲከናወን ያግዛል ። ስለሆነም በግል ዘርፉ ውስጥ ላሉ ዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች ምቹ የመሳተፊያ ሜዳ ሊመቻችላቸው ይገባል።

### ለ/ በገቢና በወጪ ንግድ ላይ የሚሳተፉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በቅንጅት አለመስራት

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የጉምሩክ ስነስርዓትን የተቀላጠፈ ማድረግ ጉልህ የሆነ አስተዋፆ የሚኖረው ሲሆን ለዚህም በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን አንድ በአንድ መቅረፍ ያሻል። ከጉምሩክ አገልገሎት አሰጣጥ በተያያዘ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከተለያዩ የባለ ደርሻ አካላት ጋር የሚሰራ ተቋም ሲሆን ከነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ግን ጠንካራ ሊባል የሚችል አይደለም። ምንም እንኳ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በገቢና በወጪ ንግድ የጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም ላይ የጎላ ድርሻ ቢኖረውም እንደ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሁሉ ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች የራሳቸውን ቀጥጥር የሚያደርጉበት አካሄድ አለ። በዚህ ሁኔታ ከሚሳተፉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- የግበርና ሚኒስቴር
- የተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ የምግብ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አሰተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
- የብሄራዊ ባንክ
- የንግድ ሚኒስቴር
- የትራንስፖርት ሚኒስቴር
- የደረቅ ወደቦች አስተዳደር

ከላይ የተዘረዘሩት የአስፈጻሚ አካላት በአንድም በሌላም መልኩ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እንዲሁም በሚወጡ ምርቶች ላይ የቁጥጥር ስራ ያከናውናሉ። ይህ ቁጥጥርም በተቻለ መጠን የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ፤ የአካባቢ ብክለትንና በአገር ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር፤ ብሎም ሌሎች የህዝብን ጥቅም ለማስከበር የታቀደ ነው። የግል ዘርፉም መንግስት እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋል።

ይሁንና የተለያዩ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ቁጥጥራቸውን የሚፈጽሙበት አካሄድ ቅንጅት የጎደለው ስለሆነ አስመጭዎች እንዲሁም ላኪዎች የተለያዩ ሰነዶችን በመያዝ በየመስሪያ ቤቱ ፍቃድ ጥየቃ እንዲዞሩ ያስገድዳል።

የግብርና ሚኒስቴርን አሰራር እንደ ምሳሌ የወሰድን እንደሆነ የምግብን ደህንነት እንዲሁም የእንስሳትንና የእፅዋትን ጤንነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእንስሳትና የእፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት(SPS Certificate) ለአስመጪዎች ይሰጣል። ስለሆነም የቁም ከብት፡ የእንስሳት ተዋፅኦ ፡ ምልምል ዘር ፡ ዕፅዋት ፡ የተባይ ማጥፊያና የመሳሰሉትን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም አስመጭ በቅድሚያ የቅድመ-ማስመጣት ፈቃድ (pre-import permit) ከግብርና ሚኒስቴር ሊያገኝ ይገባል። ይህ የቅድመ-ማስመጣት ፈቃድ የንግድ ሚኒስቴር ከሚጠይቀው የንግድ ፈቃድ በተጨማሪ የሚጠየቅ ፍቃድ ነው።

አንድ አስመጪ ለምሳሌ የተባይ ማጥፊያ እንዲያመጣ የቅድመ-ማስመጣት ፈቃድ ቢሰጠውና ይህንንም እቃ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ቢችል፤ የተጠቀሰው እቃ ጉምሩክ እንደደረሰ በግብርና ሚኒስቴር ቀርቦ የማስለቀቂያ ፍቃድ (import authorization) እንዲሰጠው በማመልከቻ ይጠይቃል። ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ የሚገባቸው ሰነዶች አሉ። እነዚህም፡

- የቅድመ-ማስመጣት ፈቃድ (pre-import permit)
- የማጓጓዣ ሰነድ እና
- የዋጋ ሰነድ ናቸው።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩት ሰነዶች በማያያዝ ለግብርና ሚኒስቴር ፍተሻ (inspection) እንዲደረግለት ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ማመልከቻም እንደቀረበ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያ መድቦ እቃው በሚገኝበት የጉምሩክ ጣቢያ ተገኝቶ የፍተሻ ስራውን እንዲያካሂድ ያደርጋል። ይህ ፍተሻም ከጭነቱ የተወሰነውን ያህል በማየት ይካሄዳል። የገባው እቃም በህግ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላቱን ሲረጋገጥ ለአስመጭው የማስለቀቂያ ፍቃድ (import authorization) እንዲሰጠው ይደረጋል። ይህን የማስለቀቂያ ፍቃድ የተሰጠው አስመጪም ፍቃዱን ለጉምሩክ በማቅረብ እቃው እንዲለቀቅ ያደርጋል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ዓይነት የፍተሻና የቁጥጥር ስርዓት ሌሎች የአስፈጻሚ አካላትም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ይፈፅማሉ። ስለሆነም እንደ ግብርና ሚኒስቴር ሁሉ በተወሰኑ እቃዎች ላይ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የቁጥጥር ስራ ያካሂዳሉ። ስርዓቱም ከሞላ ጎደል ከላይ በተዘረዘረው መልኩ የሚፈጸም ነው። በተመሳሳይ የንግድ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ያወጣቻቸው አስገዳጅ ደረጃዎች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ

እቃዎች  ማሟላታቸውን ያረጋግጣል። ይህንንም ለመወጣት የንግድ ሚኒስቴር የራሱ የሆነ የፍተሻ ላብራቶሪ ስለሌለው በቅንጅት ከ ኢትዮጵያ የተሰማሚነት ምዘና ድርጅት (Confromity Assessment Agency) ጋር አብሮ ይሰራል።

ምንም እንኳ ከላይ የተገለጸው የፍተሻ ስርዓት ብዙ ቀናት ይፈጃል የሚባል ባይሆንም አስመጪዎችም ሆኑ ላኪዎች ከጉምሩክ ጣቢያ ወደሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች በመመላለስም ሆነ ሰነድ በማባዛት የሚጠፋው ግዜና ገንዘብ ጉዳዩ በተቀላጠፈና በቀላል ወጪ ብሎም ወረቀት-አልባ /paperless/ ሥነሥርዓት እንዳይፈጸም ያደርጋል።

እዚህ ላይ የሌሎች አገራትን ልምድ ማየት የሚበጅ ይሆናል።

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ አገራት የህዝብን ብሎም የዕፅዋትን ጤንነት ለመጠበቅ ሲሉ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እንዲሁም ከአገር ውጪ በሚወጡ እቃዎች ላይ የተለያዩ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ፍተሻና ቁጥጥር ያካሂዳሉ። ይህንን የሚፈጽሙበት እጅግ የተቀናጀና በቀላል ወጪ የሚካሄድባት  ሥነሥርዓትን ዘርግተዋል። በርግጥ ይህንን የአንድ መስኮት አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ ብቁ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ መጠቀም ያሻል። በአገራችን አሁን ተግባራዊ እየሆነ ያለው አሰራር ደንበኞች የጉምሩክ ሥነሥርዓት ለመፈጸም ወደሚመለከታቸው መ/ቤቶች በአካል መገኘት ሲጠበቅባቸው ይህ ወደ ተለያዮ መ/ቤቶች የመሄድ ሁኔታም ጊዜም ሆነ ገንዘብ እንደሚያባክን ከላይ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው። እንዲህ አይነት ሁኔታ ለማስቀረት የተለያዮ አገራት ጉዳዮች በአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲያልቁ የሚያደርጉበት አሰራር (single window processing) ዘርግተዋል። ይህም አሰራር ቀደም ብሎ ተግባራዊ የሆነው በሲንጋፖር ሲሆን በአሁኑ ግዜ በብዙ አገራት ተቀባይነት አግኝቶ በአህጉራችንም ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል። ለዚህም በቅድሚያ ከሚጠቀሱት አገራት መካከል ጋና ትገኝበታለች።

በዚህ አሰራር ብዙ አገራት አመርቂ የሚባል ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን ደንበኞች ከአንድ ኤጀንሲ ወደ ሌላኛው ሰነዶችን እየያዙ የሚሄዱበትን አሰራር ያስቀራል። ይልቁንም የሚመለከታቸው መ/ቤቶች በየጉምሩክ ጣቢያዎች የራሳቸውን ሰራተኛ መድበው ከማሰራታቸውም በላይ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ መጠይቆች ለየሚመለከታቸው መ/ቤቶች ቀደም ብሎ ኤሌክትሮኒካል በሆነ መንገድ እንዲበተኑ ይደረጋል። እነዚህን ሰነዶች በመመልከት በየጉምሩክ ጣቢያ የሚገኙት የየመስሪያ ቤቶች ተወካዮች አስፈላጊውን ፍተሻ በመፈጸም ፍቃድ የመስጠት አገልግሎት ይሰጣሉ። የሰራተኞች በየጉምሩክ ጣቢያው መገኘት ደንበኞች በየመስሪያ ቤቱ እየሄዱ ፍተሻ እንዲካሄድላቸው የመጠየቅን ስራ ያስቀራል።

በኢትዮጵያ ያለው አሰራር ግን ቅንጅት ከማጣቱም ባሻገር ከጉምሩክ ውስጣዊ አሰራር አለመጠናከር ጋር ተደምሮ በአሁኑ ሰዓት የጉምሩክ ሥነሥርዓት የቴክኒክ ቁጥጥር ብቻ ለመጨረስ በአማካይ 5 ቀናት ያህል ከመፍጀቱም በላይ ይህንን ስርዓት ለመፈጸምም እስከ 5100 ብር ሊያስወጣ እንደሚችል በግል ዘርፍ ማበልጸጊያ ማዕከል በጉምሩክ ስርዓት ዙሪያ የተደረገው ጥናት ያመለክታል። ይህ ቁጥርም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈጀውን ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ወደ ውጪ ለመላክም 4 ቀናት ያህል የሚፈጅ ሆኖ በገንዘብ እስከ 2580 ብር ያህል ያስወጣል። ይህ አሰራር ከዚህ በተሻለ ቢቀናጅ ይህንን አላስፈላጊ ወጪ ከማስቀረቱም በላይ እየወሰደ ያለውን ጊዜ በግማሽ ሊቀንሰው ይችላል።

## ሐ/ ከጉምሩክ ቀረጥ አወሳሰን ጋር ተያይዞ የሚደርሱ መዘግየቶች

በዚህ ነጥብ ስር ለማንሳት የተፈለገው ጉምሩክ የሚጠቀምበት የቀረጥ አተማመን ዘዴ ሳይሆን ከእርሱ ጋር ተያይዞ የሚደርሱ መዘግየቶች ናቸው። በእርግጥ አሁን በስራ ላይ ያለው የጉምሩክ ቀረጥ አተማመን ከፍተኛ የሆነ አቤቱታ የሚቀርብበት ቢሆንም ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ባለስልጣኑ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ በትጋት እየሰራ ያለበት ሁኔታ ስላለ እርሱን በዚህ ጥናት ለማካተት አልተፈለገም።

- **ለቀረጥ ምደባ የላብራቶሪ ፍተሻ በሚያስፈልግበት ግዜ ይህን ፍተሻ በፍጥነት አለመተግበር**

በጉምሩክ የቀረጥ ምደባ ዙሪያ (customs tariff classification) ከሚነሱት ችግሮች መካከል ይህንኑ ምደባ ለመፈጸም አስፈላጊውን የላብራቶሪ ፍተሻ ከማካሄድ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን መዘግየት መዳሰስ አስፈላጊ ነው። ጉምሩክ አንድ እቃ በየትኛው የቀረጥ መደብ ውስጥ ይወድቃል የሚለውን ለመወሰን ከሚጠቀምቸው መስፈርቶች መካከል የእቃው የኬሚካል ይዘት አንዱ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአስመጪዎችና በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት መካከል ብዙ ግዜ አለመግባባት ይከሰታል። ይህ አለመግባባት ከሚከሰትባቸው እቃዎች መካከል የጁስ ምርቶች፡ አንዳንድ ኬሚካሎች እንዲሁም የጨርቅና የአልባሳት ምርቶች ይገኙበታል። ይህም ልዩነት የሚፈጠረው አስመጪው የእቃው አይነት ሊያስመድበው የሚገባው ዝቅ ባለው የቀረጥ መደብ ነው ሲል፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደግሞ አይደለም የዚህ እቃ ምድብ መሆን ያለበት ከፍ ባለው የቀረጥ ምድብ ነው በሚልበት ግዜ ነው። የጁስ ምርቶችን እንደ ምሳሌ የወሰድን እንደሆነ አንድ ተፈጥሮአዊ የጁስ ምርት /ኦርጋኒክ / የሚጣልበት የቀረጥ መጠን ዜሮ ሲሆን በሰው ሰራሽ ሁኔታ ሌላ ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉት ደግሞ እስከ 30 ፐርሰንት እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።

ይህ አይነት ልዩነት በሚፈጠርበት ወቅት ጉምሩክ እቃው በመጋዘን እንዳለ አስፈላጊውን የተስማሚነት ምዘና እንዲፈጸምበት ያዝዛል። ይህ አገልግሎት ግን በጉምሩክ ስለማይሰጥ ምዘናው በዕቃው ላይ በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት እስኪፈጸም ድረስ ደንበኞች እቃቸው ባለመለቀቁ ምክንያት

ከመጉላላታቸውም በላይ ለተጨማሪ የመጋዘን ኪራይ ይዳረጋሉ። አሁን እየተተገበረበት ያለው አሰራር እንደሚያሳየው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስለጣን ለተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ ደብዳቤ ይጽፋል ፡ በደብዳቤውም የተጠቀሰው እቃ የተስማሚነት ፍተሻ ይደረግበት ዘንድ ይጠይቃል። ነገርግን ኤጀንሲው ይህን የምዘና ተግባር በሚፈለገው ፍጥነት አይፈጽምም። በዚህም ምክንያት አስመጪው ነጋዴ ላላስፈላጊ ወጪ ይዳረጋል። እንደሚታወቀው እነዚህና መሰል ወጪዎች በመጨረሻ ለሸማቹ ማህበረሰብ በዚያው ልክ እዋጋ ላይ በጭማሪ ይቀጠላል። ይህም በአገሪቱ ውስጥ የሚታየውን የገበያ ግሽበት በማባባስ ረገድ የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ።

- **የቀረጥ ምደባን በአግባቡ ስለመፈጸሙ የሚያረጋግጡ ቴክኒካዊ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች በበቂ ጥራትና ብዛት አለመኖር**

በዘረፉ የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት እንደሚያስረዱት ትራንዚተሮች በዲክላራሲዮን ላይ ያሰፈሩት የቀረጥ ምደባ በትክክል ስለመቀመጡ ለመወሰን የተራዘመ ግዜ የሚወስድበት ምክንያት አንድም በጉምሩክ ይህንን ለመተግበር የተሰማሩ ባለሙያዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን ሲሆን ፤ አሊያም አንዳንድ ባለሙያዎች ዕቃዎች ላይ ያላቸው እውቀት ውስን መሆን ነው፡፡ በተለይ የኬሚካል ውጤቶችን በመመደብ ሂደት የሚያጋጥመው ችግር ቀላል የሚባል አይደለም።

በግል ዘርፍ ማበልፀጊያ ማዕከል የተሰራው ጥናት እንደሚጠቁመው ይህንን የቀረጥ ምደባ ጉዳይ ለመፈጸም ብቻ እስከ 3 ቀናት የሚፈጅበት ግዜ አለ። አንድ የተከፈተ ኮንቴይነር አሰፈላጊውን ፈተሻ አጠናቆ እስኪወጣ ድረስ ደግሞ በአሰራር ሌላ ኮንቴይነር ፍተሻ መጀመር አይቻልም። ስለዚህ በአንድ ጭነት ላይ የሚደርስ መዘግየት በሌሎችም ተመሳሳይ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም።

- **የጉምሩክ የዋጋ ዳታ ቤዝ ውስንነት**

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር በጉምሩክ በተያዘው የዋጋ ዳታ ቤዝ አንድ ዕቃ በግልጽ ሰፍሮ በማይገኝበት ግዜ ይህንን ለመወሰን እስከ ሳምንት ድረስ የሚወስድበት አጋጣሚ ቀላል የሚባል አይደለም። ይህም ችግር የሚከሰተው በዋነኛነት የጉምሩክ የዋጋ ዳታ ቤዝ በየጊዜውና በተከታታይ ሰለማይደራጅ ነው። ይህ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት አስፈላጊውን የትርጉም ውሳኔና አመራር ለማግኘት ጉዳዩ ወደ ለሚመለከተው ክፍል ይመራል። ውሳኔ በአፋጣኝ የማይሰጥ ስለሆነም አስመጪዎች ላላስፈላጊ የመጋዘን ኪራይ እና ሌሎች ወጪዎች ይዳረጋሉ።

**መ. የስጋት ስራ አመራር / risk management/ ትግበራ የተፈለገውን ያህል ፍጥነት አለማስገኘቱ**

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የስጋት ስራ አመራር መርህን በመከተል ጭነቶችን እንደ ስጋት መጠናቸው ቀይ ፣ ቢጫና አረንጓዴ በሚል ቀለማዊ ሥርዓት የሚመድብ ሲሆን በቀይ መደብ ውስጥ የሚወድቁ የሰነድ እንዲሁም የእቃ ፍተሻ ሲደረግባቸው ቢጫ መደብ ውስጥ የሚወድቁ ደግሞ የሰነድ ፍተሻ ብቻ ተፈጽሞባቸው እንዲያልፉ ይደረጋል። አረንጓዴ መደብ ውስጥ የሚወድቁ ጭነቶችን የወሰድን እንደሆነ የሰነድም ሆነ የእቃ ፍተሻ ሳይፈጸምባቸው የጉምሩክ ስነስርዓት አጠናቀው የሚወጡበት አሰራርን ጉምሩክ መተግበር ከጀመረ ውሎ አድሯል። ይህንን ምደባ ለመፈጸም ጉምሩክ ወደ ስምንት የሚደርሱ መስፈርቶችን ይጠቀማል። እነዚህም፡ የዕቃው ዋጋ፤ የዕቃው ቀረጥ መጠን፤ የአስመጪው የቀደመ ታሪክ፤ የጉምሩክ አስተላላፊው የቀደመ ታሪክ፤ ዕቃው የተሰራበት አገር፡ ዕቃው የተጫነበት አገር፤ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ኮድ፤ ልዩ መስፍርቶች ማሟላት ያለባቸው ናቸው። እነዚህ ግብዓቶችን በመጠቀም የዕቃዎች ቀይ ፣ ቢጫ ወይም አረንጓዴ መሆን ይወሰናል። እነዚህ መስፈርቶች አብዛኛዎች ከአስመጪው ቁጥጥር ውጭ ናቸው። በመሆኑም በታማኝነት የሚሰራ አስመጪ ዕቃው በቀይ ወይም በቢጫ መደብ የማለፍ ዕድል ከፍ ያለ ነው። በዚህም የተነሳ ይህ አሰራር የተፈለገውን ያህል እርቀት እየሄደ አይገኝም ። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ከ60-75 % የሚሆነው ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ጭነት በቀይ ምድብ ውስጥ የሚያልፍ ሲሆን ይህም በተግባር ላለው የተንዛዛ የጉምሩክ አሰራር ከፈተኛ አሰተዋጾ አለው። በአሁኑ ግዜ በአረንጓዴ መደብ ውስጥ የሚያልፍው በአብዛኛው የመንግስት ጭነት ሲሆን ይህን አሰራር እንደገና በመቃኘት በሪከርዳቸው አስተማማኝ የሚባሉ ኩባንያዎች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ወደ ቢጫ አልፎም ወደ አረንጓዴ የሚገቡበት አሰራርን ማዳበር ይገባል።

ከዚህ በሻገር በቀይ መደብ ውስጥ የሚያልፉ ዕቃዎች የሰነድም ሆነ የዕቃ ዝርዝር ፍተሻ ይደረግባቸዋል። የዕቃ ፍተሻ ማለት የዕቃውን የስሪት አገር፤የመጣበትን አገር ፤ ባህሪ፤ ሁኔታ፤ አይነት፤ ብዛት፤ዋጋ፤የታሪፍ አመዳደብ፤ በዕቃ ማሳወቂያ ዲክላራሲዮን ቅጽ ውስጥ በቀረበው ዝርዝር መሰረት የተሟላ መሆኑን በጉምሩክ የሚፈጸም አካላዊ ምርመራ ነው።የዚህ ፍተሻ ሰዓትም ስታንዳርድ ባለመቀመጡ የተንዛዛና የዘገየ የፍተሻ ሥርዓት ይታያል።

**ሠ. በግዜያዊነት ለፕሮጀክት ስራ ገብተው ተመልሰው ከሚወጡ የገቢ ዕቃዎች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች**

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ሕግ በሚያዝዘው መሰረት ከግንባት ስራና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ለመፈጸም የተለያዩ የፕሮጀክት ዕቃዎች በግዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ሊገቡ ይችላሉ። እነዚህ ዕቃዎች የመጡበት ምክንያት እንደተጠናቀቀ በመጡበት አኳኋን ሊወጡ ይገባል ። ስለሆነም እነዚህ ቀረጥ

ሳይከፈልባቸው በግዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ተመልሰው መውጣታቸውን ለማረጋገጥ ብሎም ለመንግስት ሊከፈል የሚገባ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ መከፈሉን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ ዋስትና ሊጠይቅ ይችላል። ለምሳሌ በግዚያዊነት ገብተው ተመልሰው በሚወጡ ያገለገሉ ዕቃዎች እርጅና ዋጋ ላይ ዕቃዎች ሲወጡ ባለው ታሪፍ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል። ከላይ የተጠቀሰው ዋስትና የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ወይም የባንክ የዋስትና ሰነድ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊሆን ይችላል።

ይሁንና ከዚህ ጋር በተያያዘ የጭነት አስተላላፊዎችን ለከፍተኛ ኪሳራ የሚዳርግ አሰራር አለ፡፡ ምንም እንኳ ከፕሮጀክት ስራዎች ጋር በተያያዘ በግዚያዊነት ከቀረጥና ታክስ ክፍያ ነጻ ሆነው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ የዋሉበት ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የፕሮጀክቱ ባለቤት ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ ቢኖርበትም ይህን ሳይፈጽም ወይም በግዜያዊነት የገባው ዕቃ ሲወጣ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ማግኘት ሳይችል ሲቀር በወቅቱ ዕቃውን ያስገባው የጭነት አስተላላፊ እንደ ወኪል ተቆጥሮ በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ጎድሎ ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ግዜ ውስጥ ከፈሉ የሚልበት አሰራር አለ። በዚህም የተነሳ የጭነት አስተላላፊዎች የዕቃውን ባለቤት መጠየቅ በማይችሉበት ሁኔታ ላልተጠበቀ ኪሳራ ይዳረጋሉ።

### ረ. የመጋዘን ጥበትና ተያያዥ ጉዳዮች

የጉምሩክ ስነስርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከወደብ የመጣ ጭነት በጉምሩክ ጣቢያዎች እንዲቆይ ይደረጋል። በተለይም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ በኩል እጅግ ብዙ ሊባል የሚችል እቃ ያልፋል። በዚህ የጉምሩክ ጣቢያ በሚቆይበት ግዜ እቃው መራገፍ አለበት። ይህ በማይሆን ግዜ ግን አስመጪው የመኪናም ሆነ የኮንቴይነር ክራይ ይቆጥርበታል። ይህንን ለመከላከል እንዳይሆን የጉምሩክ መ/ቤት ከኮሜት የትራንስፖርት አክሲዮን ማሕበር ጋር አብሮ በመስራት ይህን መሰል ወጪ ለማስቀረት ጥረት ያደርጋል። ማሕበሩ እንደ የመንግስት የልማት ድርጅት የሚተዳደር ሲሆን የመካዘን ኪራይ ፡ የመጫንና የማውረድ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል።

በአሁኑ ግዜ ኮሜት ግልጽና ወደ ስምንት የሚደርሱ ዝግ መጋዘኖች ያሉት ሲሆን ጭነቱ ከመኪና ሳይወርድ ፈተሻ ሊካሄድበት የሚያስችል ሰፊ ቦታም አለው። በተመሳሳይም የመጫንና የማውረድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ፎርክ ሊፍቶች አሉት። ይህንንም በመጠቀም የመካዘን ኪራይ እንዲሁም የመጫንና የማውረድ አገልግሎት ይሰጣል።

ሆኖም ከኮሜት አሰራር ጋርም በተያያዘ የነጋዴው ማህበረሰብ መጉላላት ይከሰትብናል ሲል ይደመጣል ፡፡ በርግጥም የኮሜት ሃላፊዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ መጉላላት እንደሚከሰት የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ ከኮሜት አሰራር ጋር ምን ዓይነት መጉላላት እየተከሰተ ነው? ለሚለው ጥያቄ በሚቀጥለው መልክ ዝርዝር አቅርበናል፡፡

- **የመጋዘን ጥበት**

ምንም እንኳ ኮሜት ሰፊ ሊባል የሚችል የመካዘን አገልግሎት እየሰጠ ቢገኝም፡ በየግዜው የሚያጋጥመው የመጋዘን ጥበት ግን በተለይ አሰመጪዎችን እጅጉን ለኪሳራ የሚዳርግ እንደሆነ በቀላሉ የሚስተዋል ችግር ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ዋነኛ ምክንያት ኮንቴነር ጭኖ የመጣው መኪና ጭነት ባለመራገፉ ምክንያት በጉምሩክ ጣቢያ ውሎ በሚያድርበት ግዜ አስመጭው ለመኪናው ባለቤት በቀን በአማካኝ እስከ 1500 ብር ድረስ ለማውጣት መገደዱ ነው፡፡ ይህ ወጪ የነጋዴውን ተወዳዳሪነት እጅጉን ከመጉዳቱም ባሻገር ይህና መሰል ወጪዎች ወደ ሸማቹ ማህበረሰብ እንደሚተላለፉ ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ በአገሪቱ ያለውን የደረቅ ጭነት ችግርም ያባብሰዋል፡፡

በዚህ የመካዘን ጥበት ምክንያት መኪኖቻቸው በጉምሩክ ጣቢያ የሚቆምባቸው ባለቤቶች በዚህ አሰራር ለኪሳራ እንደሚዳረጉ ይገልጻሉ፡፡ ምንም እንኳ አስመጭው በቀን በአማካኝ እስከ 1500 ብር ድረስ ቢከፈልም መኪኖች ተመልሰው ሄደው ሌላ ጭነት ቢያመጡ ሊያገኙ የሚችሉትን ያህል ግን አይደርስም፡፡ ስለሆነም የዚህ አሰራር የተቀላጠፈ መሆን ሁሉንም ወገን በእጅጉ የሚጠቅም ጉዳይ ነው፡፡

- **የፎርክ ሊፍቶች በበቂ ቁጥርና ጥራት አለመኖር**

የተለያዩ ዕቃዎችን ከውጭ አገር የሚያስመጡ ኩባንያዎች ከሚማረሩባቸው ጉዳዮች መካከል በኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር የሚሰጠው የመጫንና የማውረድ አገልግሎት ተጠቃሽ ነው፡፡ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የኮሜት አክሲዮን ማህበር ከሚሰጣቸው አገልገሎቶች መካከል ፎርክሊፍቶችን እንዲሁም የሰው የሃይል በመጠቀም ኮንቴይነሮችን እንዲሁም እቃዎችን የማውረድና የመጫን አገልግሎት ነው፡፡ይህ አገልገሎት ግን በተለያየ ግዜ የሚሰናከልበት አጋጣሚዎች ከመኖሩም በላይ አገልገሎቱ በአጠቃላይ አጥጋቢ አይደለም ሲሉ ነጋዴዎች ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቅሱት የእቃ ማውረጃ ክሬን ቁጥርም ሆነ ጥራት በቂ አለመሆኑና፤ በተመሳሳይም በሰው ሃይል ለሚሰራውም የማውረድና የመጫን አገልግሎት በቂ የሰው ሃይል ባለመኖሩ የስራ መጓተት መከሰቱ ነው፡፡

በአሁኑ ግዜ ኮሜት ወደ አምስት የሚደርሱ ትላልቅ ኮንቴነሮችን የሚጭኑና የሚያወርዱ ፎረክሊፍቶች ሲኖሩት ወደ አስር የሚደርሱ ደግሞ እቃዎችን ወደ ኮንቴነር የሚጭኑና የሚያወርዱ ክሬኖች አሉት። የሚመለከታቸው የኮሜት ሃላፊዎች ከዚህ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን አልፎ አልፎ የሚያጋጥም መሆኑን ሲያስረዱ አክለውም የችግሩንም ሁኔታ የተወሰኑ ወቅቶች ላይ ብቻ የሚከሰት እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህም ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው በአመት በዓላት አካባቢ ነጋዴው ብዙ እቃ ስለሚያስመጣ እንደሆነ ይገልጻሉ። የክሬን ብልሽት ሲደርስም ደንበኞች ክሬን እየተከራዮ እያመጡ ስራውን እንደሚያስኬዱም ሳይገልጹ አላለፉም ። አንዳንዶም አስመጪዎች ክሬን ከግለሰብ ተከራይተው ለመስራት ተገደዋል። ይህም ,በአንድ ኮንቴይነር እስከ2700 ብር ያስወጣቸዋል።

እንደ መስሪያ ቤቱ ገለጻ የማሽነሪዎች ቁጥር አነስተኛ የሆነው አንድ ፎርክሊፍት እስከ 15 ሚሊዮን ብር ድረስ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ማሽነሪዎች ሲበላሹ የጥገና እቃ አቅርቦት ባለመኖሩ የተነሳ ለብዙ ግዜ ስራ ፈትተው ይቆያሉ።

የነጋዴው ማህበረሰብ በበኩሉ ይህ ጉዳይ እጅግ እንዳማረረው በተደጋጋሚ ይገልጻል። ከክሬን ቁጥር ማነስ በተጨማሪ የክሬን ብልሽት ሲያጋጥም ነጋዴዎችን ከፍተኛ ለሆነ አላግባብ ወጪ እንደሚዳርጋቸው መረዳት ተችሏል። ከዚህ ጎን ለጎን ባለስልጣኑ ሊያደርግ የሚገባውን ፍተሻ ባለማካሄዱ የተነሳ የንግድ እንቅስቃሰው ሲይስተጓጎል ይታያል። ለማጠቃለል አገር ውስጥ የገባ እቃ በአስፈላጊው ግዜና ወቅት ለገበያ መቅረብ ሳይችል መቅረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነጋዴዎች ለተጨማሪ የመኪና እንዲሁም የመጋዘን ኪራይ ይጋለጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ እቃ ወደ መጋዘን የሚያጉዝ የሰው ሃይል እጥረትም ይታያል ። ይህም ከላይ የተጠቀሰውን ችግር ያባብሰዋል ።

### ሰ. ከ CIQ ሰርቲፊኬት ትግበራ ጋር የሚነሱ አቤቱታዎች

መንግስት ከቻይና የሚገቡ ምርቶች ጥራትና ደረጃን ለመቆጣጠር እንዲያስችለው በማሰብ የቅድመ ምርመራ ተደረጎባቸው ከቻይና CIQ ሰርትፊኬት እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ። ይህ አሰራርም ተግባራዊ መሆን የጀመረው በኢትዮጵያ የንግድ ሚኒስቴርና በቻይና የፍተሻና የኳራንቲን ቢሮ /China Inspection and Quarantine Bureau (CIQ) / መሃከል በተደረሰ ስምምነት አማካኝነት ነው። ይህም እ.አ.አ. ከ ጃንዋሪ 1 2007 ጀምሮ ሲተገበር ቆይቷል።በዚህ ስምምነትም የቻይና የፍተሻና የኳራንቲን ቢሮ ከቻይና ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ አስፈላጊውን ፍተሻ ካካሄደ በኋላ የጥራት ማረጋገጫ ይሰጣል።

ይህ አሰራር ተግባረዊ እንዲሆን የተደረገው ከቻይና የሚመጡ ዕቃዎች ጥራት አስተማማኝ እንዲሆን በማሰብ ነበር ። የ CIQ ሰርትፊኬት ለማግኘት በጭነት እስከ 280 የአሜሪካ ዶላር የሚያስከፍል ሲሆን

ይህ ክፍያም አስመጪው የሚከፍለው ጠቅላላ ዋጋ ላይ ይንጸባረቃል። እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የዚህ ሰርትፊኬት አሰጣጥ ሥርዓት የታቀደለትን ግብ እየመታ ነው ወይ የሚለው ነው።

ከንግዱ ማህበረሰብና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት መረዳት እንደተቻለው የዚህ አሰራር መዘርጋት የታሰበለትን ግብ እያስገኘ አይደለም። ይህም የሆነው ይህን ሰርትፊኬት እየሰጠ ያለው የቻይና ድርጅት አግባብ ያለውን ፍተሻ በተገቢው ሁኔታ የማይፈጽም ሲሆን አሰራሩም ለሙስና የተጋለጠ ነው። ስለሆነም በህግ ከሚጠበቀው 280 የአሜሪካ ዶላር በላይ ፍተሻ ለሚፈጽሙ ባለሙያዎች ገንዘብ መክፈል የግድ ይላል። ይህም አስመጪዎችን ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉም በላይ በቅድሚያ የታሰበለትን አላማም እንዳይሳካ እያደረገ ይገኛል። ከዚህም ባሻገር አንዳንድ የታወቁ የቻይና ኩባንያዎች በዚህ ስርዓት ላለማለፍ ለኢትዮጵያ አስመጪዎች እቃ አንሸጥም እስከ ማለት ይደርሳሉ። ይህም ጥራት ያለው ዕቃ ለማስገባት ለሚፈልጉ አስመጪዎች ዕንቅፋት ሆኗል።

ይህ አሰራር በቂ የጥራት ቁጥጥር ማድረጊያ መሳሪያ እንዳልሆነ የሚጠቅሱ የዘርፉ ተሳታፊዎች የቻይና ምርት የሆነ ዕቃ ከዱባይ በሚመጣበት ግዜ የCIQ ሰርትፊኬት አቅርቡ የማይባል መሆኑ ለአሰራሩ ወጥነት ማጣት በአብነት ይጠቅሳሉ።

## ሸ. ከሰነድ መጠይቆች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋም እና አሰራሩን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ መሠረት አንድ አስመጪ ዕቃ ወደ ሃገሪቱ ሲያስገባ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፦

1. የማጓጓዣ ሰነድ

2. የዋጋ ሰነድ

3 .የባንክ ፍቃድ

4. የዕቃ ዝርዝር

5 .የተመረተበት አገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ሌሎች ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸዉ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ናቸው።

ከላይ በሕጉ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ አንድ አስመጪ የጉምሩክ ዲክላራሲዮንና የፍሬ ነገር መግለጫ በሚቀርብበት ግዜ የሚከተሉት ሰነዶችን እንዲያቀርብ ይጠየቃል፤

1 .የግብር መለያ ቁጥር

2. የንግድ ፈቃድ ፎቶኮፒ

3 .የአስመጪ ፈቃድ ፎቶኮፒ

ከዚህም በተጨማሪ ከቀረጥ ነጻ እቃ ወደ አገር ዉስጥ በሚገባበት ጊዜ ተጨማሪ ደብዳቤ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ያስፈልጋል።

የግል ዘርፍ ማበልጸጊያ ማዕከል ከላይ በተጠቀሰው ጥናቱ እንዳሰፈረው ቀላል ሊባሉ የሚችሉ የዕቃ ማስገባት ሂደቶች እነዚህንና ለጉምሩክ ሥነሥርዓት የሚያስፈልጉ ሌሎች ሰነዶችን በትጋት አዘጋጅቶ ለማቅረብ በአማካይ እስከ 8 ቀናት ይፈጃል። ይህም አመልካቾች በእንቅስቃሴ የሚያባክኑትን ጊዜ ሳይጨምር ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የሰነድ ማዘጋጀት በጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም መፍጠን ወይም መጓተት ላይ ከፍተኛ የሆነ ድርሻ ያለው መሆኑን ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሰነድ በማዘጋጀት የሚጠፋው ግዜና ገንዘብ የግሉን ዘርፍ አለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪነት በእጅጉ ሊጎዳው ይችላል። ይህ ማለት ግን ሰነደ-አልባ የጉምሩክ ሥነሥርዓት አፈጻጸም በአፋጣኝ ይዘርጋ ማለት አይደለም። ይልቁንም ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከሚጠይቃቸው ሰነዶች መካከል ላያስፈልጉ የሚችሉ ካሉ እነዚህን የሰነድ መጠይቆች ማስቀረት ይቻላል የሚለውን መከራከሪያ ለማቅረብ ነው።

አንድ አስመጪ ወይም ላኪ እቃውን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ከስምንት ያላነሱ ሰነዶችን እንዲያቀርብ ይገደዳል። በርግጥም የአብዛኛዎቹ ሰነዶች አስፈላጊነት አጠያያቂ ባይሆንም በአቀራረብ ደረጃ ግን አሁን ካለው አሰራር በተቀናጀና በተሳለጠ መልኩ ሊከናወን  የሚቻልበት ሁኔታ ይታያል። ከነዚህም ለአብነት የግብር መለያ ቁጥርንና የንግድ ፈቃድ ፎቶኮፒን መውሰድ ይቻላል። አንድ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ለመፈፀም እነዚህ ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው። በአንድ ዓመት ግዜ ወይም በወራት ዕድሜ ከአንድ ጊዜ በላይ ዕቃ የሚያስገባ ነጋዴ ካለ እነዚህን ሰነዶች በድጋሚ ለጉምሩክ እንዲያቀርብ ይገደዳል።

እዚህ ላይ ቆም ብለን ያየን እንደሆነ የግብር መለያ ቁጥር የሚያድለው እራሱ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ሆኖ ሳለ ይህን የሰነድ መጠይቅ መቅረቡ አግባብነቱ ምኑ ላይ ነው? በተመሳሳይ የንግድ ፈቃድ የሚይሰጠው የንግድ ሚኒስቴር ፍቃድ የወሰዱ የንግድ ተቋማት ዝርዝር የያዘ ዳታ ቤዝ እያለው መጠየቁ ምን ፋይዳ አለው? ይልቁንም ይህን ዳታ ቤዝ ጉምሩክም ሊጠቀምበት የሚቻልበት አሰራር መዘርጋት አለማችን እየደረሰበት ወደ አለው የወረቀት-አልባ ንግድ ያቀርበናል። ብሎም የንግድ ማህበረሰቡ ለአላስፈላጊ ወጪ እንዳይዳረግ ያግዘዋል። የወረቀት-አልባ አሰራር እንኳ ለመተግበር ብዙ ዝግጅት

ይጠይቃል ብንል እነዚህ ሰነዶች አንዴ በአስመጪው ከቀረቡ በኋላ ደጋግሞ እንዲቀርቡ መጠየቁ አስፈላጊ አይሆንም።

## 6. የመፍትሄ ሐሳቦች

- **በግል ለተሰማሩ የዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች (freight forwarding and ship agency)በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሳተፍበትን የህግ ማዕቀፍ ማበጀት**

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት  ለተቀላጠፈና የተሳለጠ የትራንዚት አገልግሎት ብሎም ወጪ ቆጣቢ ለሆነ የንግድ ስርዓት ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ አሌ የሚባል አይደለም። ይህንንም በመገንዘብ የነጋዴው ማህበረሰብ መንግስት የጀመረውን ትግበራ ለመደገፍ ዝግጁ ነው። ይሁንና ይህ ትግበራ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በሞኖፖሊ እንዲያዝ ተደርጎ መዘርጋቱ በግል ለተሰማሩ የዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች ከገበያ መውጣትን ሊያስከትል የሚችል መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው። ይህ ደግሞ መንግስት ለማስፈጸም ላቀደው  የተቀላጠፈ የትራንስፖርትና የትራንዚት አገልግሎት የመስጠት ዓላማ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ጎን ይኖረዋል። በርግጥም ያለግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ብቻውን በበቂ ሁኔታ ይህን ስራ ሊፈጽም እንደማይችል መገመት አያዳግትም። ከዚህም ባሻገር የግል ዘርፉ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ የስራ ዕድል፣ ሊፈጥር የሚችለውን የብዛት ተፅእኖ (multiplier effect)፣ ሊያመነጭ የሚችለውን ግብርና ቀረጥ የማስቀረት አሉታዊ አንድምታ ይኖረዋል።

ስለሆነም የግል ዘርፉን በተስተካከለ የፉክክር ሜዳ ላይ ሊያሳትፍ የሚችል የህግ ማዕቀፍ ሊወጣ ይገባል። እንደ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ሁሉ በግል የተሰማሩ የዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ሊያሳትፋቸው የሚችል ህግ ማውጣት ተገቢ ነው። አንድ መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር አንድ እቃ አስተላላፊ በመልቲ ሞዳል ኦፕሬተርነት ለመሳተፍ በርግጥም  በስሙ የተመዘገበ መርከብና የየብስ ትራንስፖርትን ማከናወን የሚያስችለው የጭነት መኪኖች ሊኖሩት የግድ አይልም። ይልቁንም እነዚህን የትራንስፖርት አገልግሎቶች ከሌላ ደርጅት ሊኮናተርና ሊያቀርብ ይችላል። ስለሆነም በኢትዮጵያ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ለግል ዘርፉ ክፍት ቢሆን አገልግሎቱን ለመስጠት የኢትዮጵያ የመርከብ አገልግሎት ድርጅትን እንዲሁም ለየብስ ጉዞ ደግሞ የጭነት መኪኖች ከሌሎች ድርጅቶች ሰብ-ኮነትራክት በማድረግ የግል ኩባንያዎች ሊሰሩ ይችላሉ።

- **በገቢና በወጪ ንግድ ላይ የሚሳተፉ የመንግስት መ/ቤቶች በቅንጅትና የአንድ መስኮት አገልግሎትን መርህ በተከተለ መልኩ የሚሰሩበትን መንገድ መፍጠር**

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የተለያዩ አገራት በገቢና በወጪ ንግድ ላይ የሚሳተፉ የመንግስት መ/ቤቶች (border agencies ) በተቀናጀና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም የሚሰሩትን ስራ

የተቀላጠፈ ከማድረግ ባሻገር አስመጪዎች እንዲሁም ላኪዎች ዕቃቸውን ያለምንም እንግልት ከጉምሩክ የሚረከቡበት ሁኔታ ዘርግተዋል፡፡ ይህንንም ማሳካት የቻሉት የጋራ የሆነ ፖርታል በማዘጋጀት አስመጪው ወይም ላኪው የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ወደዚህ ፖርታል በመላክ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሙሉ አሰተያየታቸውን እንዲሁም ፈቃዳቸውን የሚሰጡ መሆኑ ሲሆን በአካል ተገኝተው መፈተሽ በሚያስፈልግበትም ወቅት ይህንኑ ተግባር በጉምሩክ ተገኝተው የሚፈጽሙ መሆናቸው ነው፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው አሰራር ግን አስመጭው ወይም ላኪው በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተገኝቶ ተመሳሳይ የሆኑ ሰነዶችን ለነዚህ የተለያዮ መ/ቤቶች አባዝቶ ማቅረብንና በነዚህ መስሪያ ቤቶች በአካል መገኘትን ይጠይቃል፡፡ ይህ አሰራር ደገሞ ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ እንደሚችል መገንዘብ ቀላል ነው፡፡

ስለሆነም አግባብነት ያለውንና አገራት እየተገበሩት የሚገኘውን የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል በጉምሩክ ስር የሚተዳደር፤ የተለያዮ ሰነዶች እንዲሁም የፍቃድ ትዕዛዞች በኤሌክትሮኒካል መንገድ የሚፈጸምበት ፖርታል ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ ሲሆን በውጭ ንግዱ ላይ በአንድም በሌላም መልኩ ሚና ያላቸውን መስሪያ ቤቶች በዚህ መልኩ እንዲፈጽሙ መደንገግን ይጠይቃል፡፡

- **ጉምሩክ የተስማሚነት ምዘና መፈጸም የሚያስችለውን የላብራቶሪ ፍተሻ በራሱ መፈጸም እንዲችል የራሱ ማዕከልን ማቋቋም**

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ከውጭ የሚገቡ ምርቶች አገባብነት ያላቸውን ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችንና ሕጋዊ መሰፈርቶች ያሟሉ መሆኑን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የመስጠት ሃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራ ይህን በመሆኑ የጉምሩክን ጥያቄ በ አፈጣኝ ምላሽ ያለመሰጠት አዝማሚያ ይታያል፡፡ በመሆኑም ባለስልጣኑ የቀረጥ አተማመንን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈፀም ያስችለው ዘንድ የራሱ የሆነ የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ማቋቋም ይኖርበታል፡፡ ይህም በቀረጥ አተማመን ዙሪያ ተያይዞ የሚነሳውን የተስማሚነት ምዘናን በቀላሉና በተቀላጠፈ ሁኔታ ማካሄድ እንዲችል ለደንበኞችም አመች ሁኔታን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ሌላው ከቀረጥ ምደባ ጋር ተያይዞ የተነሳውን የቴክኒክ ዕውቀት ማነስ እንዲሁም ይህን ስራ ለመተግበር ያለውን የባለሙያዎች እጥረት ለመፍታት አስፈላጊው ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን በቦታው መመደብ አቅማቸውን ለማጎልበት ደግሞ ተከታታይ ስልጠና መስጠት ይበጃል፡፡ በተመሳሳይም የጉምሩክ የዋጋ ዳታ ቤዝ በተቻለ መጠን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚደራጅበትና በዳታቤዝ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከውጭ

በሚገባበት ግዜ የዚህ ዕቃ ዋጋ በአፋጣኝ የሚወሰንበት ሥርዓት መዘርጋት ወሳኝነት የይኖረዋል። በዳታቤዝ ውስጥ የሌለ ዕቃ በሚገባበት ግዜ ባለስልጣኑ አስመጪው በሚያቀርበው የቻምበራይዝድ የዋጋ ሰነድ አማካኝነት የቀረጥ ትመና ሊያደርግ ይገባል።

- **የመጋዘን አገልግሎት የሚስፋፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር**

ከመጋዘን አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚደርሱ መጉላላትና ወጪዎችን በተገቢው ሁኔታ መቅረፍ እንዲያስችል ሊወሰዱ ከሚገባቸው እርምጃዎች መካካል አንዱ የግል ባለሃብቱ የመጋዘን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው። በአሁኑ ግዜ ይህን አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት የኮሜት ትረንስፖርት አክሲዮን ማህበር እና የኢትዮጵያ የደረቅ ወደቦች ድርጅቶች ናቸው። በተለይም ከመልቲሞዳል ትራንስፖርት ተግባራዊ መሆን ጋር ተያይዞ ዕቃ ከወደብ በቀጥታ ወደ ደረቅ ወደቦችና ሌሎች የጉምሩክ መጋዘን መግባት ስላለበት የመካዘን መጨናነቅ ሊፈጠር መቻሉ አይቀሬ ነው። ስለሆነም ለዚህ አገልግሎት መሳካት ጉልህ ድርሻ ስለሚኖረው የግል ዘርፉ ጎን ለጎን ሊሰራ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ወሳኝ ነው። ይህ አሰራር አግባብ የሆነውን የመንግስት ገቢ በአስተማማኝ ሁኔታ መሰብሰብ እንዲያስችል የጉምሩክ ባለስልጣን በመጋዘኖች ላይ እንዲሁም ወደ መጋዘን በገቡ ዕቃዎች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል።

- **የመጫንና የማውረድ አገልግሎት በተቀላጠፈ ሁኔታ መፈጸም**

እዚህ ላይ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር ዕቃ ከመጫንና ከማውረድ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው መስተጓጓል በቀላሉ መቅረፍ የሚቻል ጉዳይ ነው። ይህ ችግር በብዛት የሚከሰተው በቃሊቲ የጉምሩክ ጣቢያ እንደሆነ የነጋዴው ማህበረሰብ ያስረዳል። በርግጥም ይህ ጣቢያ እጅግ ብዙ የሚባል የጉምሩክ ዕቃ የሚያልፍበት ነው። ሆኖም ግን በፎርክሊፍት መበላሸትና የሰው ሃይል እጥረት በመሰሉ ቀላል ምክንያቶች ነጋዴው ለኪሳራ ሊዳረግ አይገባም። ይህንንም ችግር በዘቄታው ለመፍታት እንዲቻል የግል ዘርፉ ከመንግስት ጋር በመቀናጀት (Public Private Partnership) በየጉምሩክ ጣቢያዎች ብሎም በደረቅ ወደቦች የመጋዘን አቅርቦትና የዕቃ ማስተናገድ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ቢደረግ የሚሰጠውን አገልግሎት እጅግ የተሳለጠና የተቀላጠፈ ያደርገዋል። የግል ዘርፉ መሳተፍ ለአገልግሎቱ ስፋት ሲሰጠው የመንግስት አብሮ መስራት ደግሞ ለቁጥጥርና ሌሎች የማህበረሰቡን ጥቅም ለማስከበር ያግዛል።

ከዚህ በተጨማሪ የመጫንና የማውረድ አገልግሎት በአሁኑ ሰዓት እየሰጠ የሚገኘው የኮሜት ድርጅት ስራ በቂ ቁጥር ያላቸው ፎርክ ሊፍቶችን ሊያቀርብ ስላልቻለ የግል ዘርፉ ይህንኑ ተግባር ሊፈጽም የሚችልበትን አሰራር መዘርጋት ይገባል።

- **የስጋት ስራ አመራር / risk management/ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ መከለስ**

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት ጭነቶች በአረንጓዴ፡ ቢጫና ቀይ ይመደባሉ። ይሁንና መንግስት የዚህን አሰራር ሊፈጥር የሚችለውን ክፍተት በማሰብ ይመስላል ከ65-75% ያለነሰ ጭነት አሁንም በቀይ መደብ ውስጥ ያልፋል። ይህም በመሆኑ ብዙዎች ዕቃቸው ሙሉ ፍተሻ እስከሚካሄድባቸው ድረስ ነጋዴዎች ለከፍተኛ ወጪ ይዳረጋሉ። ይህንንም ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ ጉምሩክ በቂ መረጃ በማሰባሰብና አሁን የሚጠቀምበትን መስፈርቶች በመከለስ የስጋት ሁኔታቸው ዝቅ ብሎ የተገኙትን የተወሰኑትን ወደ ቢጫ አልፎም አረንጓዴ መደብ ውስጥ የሚወድቁበትን አሰራር ቢዘረጋ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚደርሰውን መዘግየት በእጅጉ ሊቀንሰው ይችላል። ይህ የረጅም ግዜ መፍትሄ ሊሆን ሲችል በአጭር ግዜ ግን በቀይ መደብ ውስጥ የሚያልፍ ጭነት ላይ የሚደረግ ፍተሻ በምን ያህል ግዜ ውስጥ ሊያልቅ እንደሚገባው ስታንዳርድ ግዜ ቢመደብለት ስራዎች በፍጥነት ሊሰተናገዱ ይችላሉ።

- **በግዜያዊነት ለፕሮጀክት ስራ ገብተው ተመልሰው የሚወጡ የገቢ ዕቃዎች ታክስና ቀረጥ የመክፈል ሃላፊነት ወደ ጭነት ወይም ጉምሩክ አስተላላፊዎች አለማስተላለፍ**

ከግንባት ስራና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ለመፈጸም  የተለያዩ የፕሮጀክት ዕቃዎች በግዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በሚገቡበት ግዜ እነዚህ ዕቃዎች የመጡበት ምክንያት እንደተጠናቀቀ በመጡበት አኳኋን እንዲወጡ ለማስቻል የኢትዮጵያ የጉምሩክ ሕግ በሚያዝዘው መሰረት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከዕቃዎች ባለቤት የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ወይም የባንክ የዋስትና ሰነድ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት እንደ ዋስትና ሊይዝ ይገባዋል። ከዚህ ባሻገር እነዚህ ዕቃዎች ታክስ ወይም ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የወጡ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህን ዋስትና የባለቤቱን ግዴታ ለመወጣት ሊያገለግል ይገባዋል። ከዚህ ባለፈ የጭነት አስተላላፊዎች ይህን በተመለከተ ሊጠየቁ አይገባም። ከላይ የተጠቀሰው ዋስትና እንዲያዝ ሕጉ የሚያዝዘውም ይህን መሰል ሁኔታ ሲፈጠር ሃላፊነቱን በዋስትናው ላይ ለመወጣት ነው።

- **የ CIQ ሰርቲፊኬትን ማስቀረት**

ከቻይና የሚመጡ ዕቃዎችን ጥራት ለማረጋገጥ የ CIQ ሰርትፍኬት ማግኘት እንደሚጠበቅባቸው ከላይ ያየነው ጉዳይ ነው። ይሁንና የታለመለትን ዓላማ እያሳካ ስላልሆነ የዚህን ሰርትፍኬት የማቅረብ ግዴታ ቢነሳ አስመጪዎች እየገጠማቸው ያለውን ችግር ለመቅረፍ ይስችላል።

- **ለሰነድ መጠይቆች የተሳለጠና የተቀናጀ ሥርዓት መዘርጋት**

ከሰነድ መጠይቆች ጋር ተያይዞ ከሚነሱት ችግሮች መካከል አላስፈላጊ የሰነድ መጠይቆች መኖር አንዱ ነው። በተለይም የግብር መለያ ቁጥርን፤ የንግድ ፈቃድ ፎቶኮፒ፤ እንዲሁም የአስመጪ እና ላኪ ፈቃድ ፎቶ ኮፒን በየግዜው የማቅረብ ግዴታ ፈጣንና ወጪ ቆጣቢ የጉምሩክ አሰራር ለመዘርጋት እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል አይካድም። በተለይም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የግብር መለያ ቁጥር የሚያድል እራሱ ስለሆነ ይህንኑ ከዳታቤዙ ለዚህ ተግባር ሊጠቀምበት ይችላል። በተመሳሳይ መልኩም የንግድ ሚኒስቴር የንግድ ፈቃድ ያወጡ ሰዎችን ዳታ ቤዝ የሚይዝ ስለሆነ ይህንኑ ዳታቤዝ ከጉምሩክ ጋር የሚለዋወጡበት ስርዓት ቢዘረጋ የነጋዴው ማህበረሰብ በየግዜው እነዚህን ሰነዶች ከማባዛት ይድናል። ይህም ወጪ ከመቆጠቡም በላይ ለጉምሩክ ሥርዓት የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ቁጥር በእጅጉ ይቀንሳል። ይህ ዘለቄታዊ መፍትሄ ተግባራዊ ሆኖ መረጃ በኤሌክትሮኒካል መንገድ ልውውጥ እስከሚጀመር ድረስ አስመጪዎችና ላኪዎች እነዚህን ሰነዶች አንዴ ለባለስልጣኑ መ/ቤት ካቀረቡ ባለስልጣን መ/ቤቱ እነዚህኑ ሰነዶች መላልሶ መጠቀም ስለሚችል በተደጋጋሚ የመጠየቁን ስርዓት ማስቀረት ይችላል።

## 7. መደምደሚያ

ከላይ በዝርዝር ለመዳሰስ እንደተሞከረው የጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም ሂደት የተሳለጠና የተቀላጠፈ መሆን በንግዱ አለም ለተሰማሩት እጅጉን የመጥቀሙን ያህል ለአገራችን የምጣኔ ሃብት እድገትም የጎላ ሚና ይኖረዋል። በርግጥም የዚህ አሰራር በአጭር ግዜ መጠናቀቅ መቻል የግል ዘርፉን ተወዳዳሪነት ለመጨመርም ሆነ የገበያ ግሽበትን ለመቀነስ የራሱ የሆነ አስተዋጾ ይኖረዋል። ስለሆነም ከላይ በዝርዝር የተዳሰሱትን ጉዳዮች ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አሰፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ አገራችን የተያያዘችውን የእድገት ጎዳና ከግብ ማድረስ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። የመፍትሄ ሐሳቦችንም ለማስፈጸም የግል ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነው።